የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩፻
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.100
ADDIS ABABA, 3rd August ,2016


**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፭/፪ሺ፰ ዓ.ም


ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የከፍተኛ ትምህርት የልህቀት ማዕከላት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…ገጽ ፱ሺ፩፻፺፪


**CONTENT**

Proclamation No. 975/2016


Eastern and Southern Africa Higher Education Center of Excellence Project, Ratification Proclamation ......................................................................Page 9192


## አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፭/፪ሺ፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የከፍተኛ ትምህርት የልህቀት ማዕከላት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፯ ሚሊዮን ፬፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር( አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኝ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብስባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት

## PROCLAMATION No. 975/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, a Financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount Equivalent 17,400,000 SDR (Seventeen million and four hundred thousand) Special Drawing Rights for financing the Eastern and Southern Africa Higher Education Centers of Excellence project was signed in Addis Ababa on the 15th day of June, 2016.

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 7th day of July ,2016.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with of Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የሚከተለው ታውጇል፡-



## ፩. አጭር ርዕስ

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የከፍተኛ ትምህርት የልህቀት ማዕከላት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፭/፪ሺ፰ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5794-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፯ ሚሊዮን ፬፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation maybe cited as the "Eastern and Southern Africa Higher Education Center of Excellence Project Ratification Proclamation No. 975/2016.

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit number 5794-ET signed in Addis Ababa on 15th June 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of equivalent 17,400,000 SDR (Seventeen million and four hundred thousand SDR ) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of August , 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**